# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
# አቅራቢዎች

## አታላዩ
## ያዕቆብ



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot; Lazarus; Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሻሎ የጻፈው): M. Kerr; Sarah S.

የተተረጎመው: Abel Eshetu

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2021 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


በቤተሰባችሁ
ውስጥ ሕጻን
ተወልዶ ያውቃል?
እንዴት ደስ
ይላል!



ይስሐቅና ርብቃ
የበለጠ ደስተኞች
ሳይሆኑ አልቀረም።
እግዚአብሔር
መንታ ልጆች
ሊሰጣቸው ነው።

ልጆቹም
በሆድዋ
ውስጥ ይገፋፉ
ነበር።እርስዋም
ጸለየች።
እግዚአብሔርም፥
ሁለት ወገኖች
በማኅፀንሽ ናቸው፤
ሁለቱም የተለያየ
መንግስት ይሆናሉ።



ታላቁም
ለታናሹ
ይገዛል
አላት።በተለምዶም
ታናሽ ለታላቅ ነበር
የሚገዛው። ሁለቱም
ሕጻናት ተወለዱ።



መንትዮቹ አይመሳሰሉም ነበር።በፊትም
የወጣው ቀይ ነበረ፤ ሁለንተናውም
ጠጉር ለብሶ ነበር።



ዔሳውም አደን የሚያድን ሰው ሆነ።
ያዕቆብ በቆዳው ለስላሳ ሲሆን በቤት
ውስጥ ስራ ይሰራ ነበር።ይስሐቅም
ዔሳውን ይወድ ነበር ርብቃ ግን
ያዕቆብን፤



አንድ ቀን ኤሳው ተርቦ ነበር።ዔሳውም ያዕቆብን፥ ከዚህ ከቀዩ ወጥ አብላኝ፥ አለው።



ያዕቆብም፥ በመጀመሪያ ብኵርናህን ሽጥልኝ አለው። ዔሳውም ስለ ብኩርናው አልተጨነቀም። ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠ።

እግዚአብሔር ለይስሐቅ በሌሊት ተገለጠለት፥ እንዲህም አለው፦ እኔ የአባትህ የአብርሃም አምላክ ነኝ አትፍራ፥ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና እባርክሃለሁ ዘርህን አበዛለሁ።



ዔሳው ኬጢያውያን የሆኑ ሁለት ሚስቶች አገባ። ኬጢያውያን እግዚአብሔን የማያመልኩ ነበሩ።





ይስሐቅ ሸመገለ።ዔሳውንም የጣፈጠ መብል አዘጋጅተህ አበላ ዘንድ አምጣልኝ፤ እኔም አባርክሃለው አለው።ይህ ለበኩሮች የሚሰጥ በረከት ነው። ዔሳውም ፈጥኖ...



...ሄደ።ርብቃ ግን የይስሀቅን
ወሬ ሰምታ ነበር። እርሷ
ያዕቆብ እንዲባረክ
ትፈልግ ነበር።

ርብቃም አንድ ነገር አሰበች። ይስሐቅ የሚወደውን ምግብ እያዘጋጀች ያዕቆም



የኤሳውን ልብስ ለበሰ፤ ሰውነቱንም በበግ የቆዳ ጸጉር ሸፈነው። ይስሐቅ የማየት ችግር ነበረበት፤ምናልባትም ሊያታልሉት ይችላሉ።

ያዕቆብም ምግቡን
ወደ ይስሐቅ አመጣው፤
ዳሰሰውም፥ ይህ ድምፅ
የያዕቆብ ድምፅ ነው፥
እጆች ግን የዔሳው እጆች
ናቸው አለው።ምግቡን
አቀረበለትም፥
በላም።ከበላ
በኋላም
ያዕቆብን
ባረከው።





ያዕቆብም ከአባቱ
ከይስሐቅ ፊት ከወጣ
በኋላ፤ ወዲያው
በዚያው ጊዜ ዔሳው
ከአደኑ መጥቶ
ገባ።ነፍስህም ትባርከኝ
ዘንድ ከልጁ አደን
ይብላ አለው።



ይስሐቅ እንዳታለሉት
አወቀ። ዔሳውን
በረከቴ አይቀየርም
አለው። የዔሳው ልብ
በጥላቻ ስተሞላ
ያዕቆብን ሊገለው
ይፈልግ ነበር።



ርብቃ የዔሳውን ዛቻ
ስትሰማ ያዕቆብን ወደ
አጎቱ ቤት አሸሸችው።
ወንድምህ ጥፋትህን
እስኪረሳው ድረስ በዚያ
ተቀመጥ አለችው።



ይስሀቅ ከርብቃ
ዘመዶች ሚስት
እንዲያገባ ያዕቆብን
መከረው ያዕቆብም
ወደ አጎቱ ሸሸ።

ያዕቆብም በዚያ ሌሊት ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ።ምናልባት ብቻውን ስለነበር ፈርቶ ይሆናል። እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ነበር።







እግዚአብሔር ያዕቆብን
በሚያስደንቅ ሁኔታ
ተናገረው።የአባትህ
የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ እኔ
እግዚአብሔር ነኝ ይህችን አንተ የተኛህባትን
ምድር ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁ።





የምድርም አሕዛብ ሁሉ
በአንተ በዘርህም
ይባረካሉ። ያዕቆብም
ከእንቅልፉ ተነሥቶ በእውነት እግዚአብሔር
በዚህ ስፍራ ነው፤ እኔ አላወቅሁም ነበር አለ።
ፈራ።

ላባም ያዕቆብን ሊቀበለው ሮጠ፥ አቅፎም ሳመው፥ ወደ ቤቱም አገባው። ያዕቆብም ራሔልን ወደደ፣ ስለ ራሔል



ሰባት ዓመት ላባን

አገለገለ።

በሰርጉ ቀን ላባ ያዕቆብን አታለለው።

በዚያም ቀን በራሔል ፈንታ ለምን ልያን ሰጠኸኝ? ብሎ ያዕቆብ ላባን ጠየቀው። ላባም ፦ በአገራችን ታላቂቱ እያለች፥ ታናሺቱን መዳር ተገቢ አይደለም።



ራሔልንም አግባትና ሌላ ሰባት አመት አገልግለኝ አለው። ያዕቆብ ወንደሙ ዔሳውን እንዴት እንዳታለለው ትዝ ያለው ይመስላል።



ያዕቆብ አስራ አንድ ልጆች
ነበሩት።ከረጅም አመታት
በኋላ ቤተሰቦቹን ወደ
ትውልድ አገሩ ከነዓን
መውሰድ ፈለገ።ዔሳው ግን
እንድሚገድለው ያውቃል።



አንድ ቀን እግዚአብሔር
ሂድ አለው።ያዕቆብም
ቤተሰቡንና ከብቶቹን
ይዞ ወጣ።



ዔሳውም አራት
መቶ ሰዎችን ይዞ
ሊቀበለው መጣ።ነገር
ግን ያዕቆብን
አልተበቀለውም።



ይልቁን ሮጦ ሄደና
አቀፈው። ያዕቆብና
ዔሳው እንደገና
ወዳጅ ሆኑ፤
ያዕቆብም በሰላም
መኖር ጀመረ።



አታላዩ ያዕቆብ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘፍጥረት 25-33

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16